# የከሰሩ ፖለቲከኞችና ጽንፈኞች ከአክራሪነት ወደ ለዬለት ሽብርተኝነት

**ዮናስ 08/02/13**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች አክራሪዎችና የከሰሩ ፖለቲከኞች ሃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም ግጭት ለመቀስቀስ ሲሞክሩ ማየትና መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡ ሃይማኖትን በሽፋንነት ለመጠቀም የቆረጡት እነዚህ ወገኖች በሀገራችን ለሃይማኖት እኩነትና ነፃነት የተፈጠረውን አመቺ ህጋዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በመጠቀምና የመንግስትን ቻይነት አንደድክመት በመቁጠር በአደባባይ ህግን ተላላፊው እስከ መንቀሳቀስ ደርሰዋል፡፡ ቀላል በማይባል ደረጃ ብዥታና መደናገርን እየፈጠሩ ህብረተሰቡን በሃይማኖት ሳቢያ ወደሚቀሰቅስ ግጭት ለመምራት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በተለይ በዚህ በረመዳን የፆም ወቅት በርከት ያሉና ስርአተ አልበኝነት የተጠናወታቸው የከሰሩ ፖለቲከኞችና አክራሪዎች እንዳሻቸው እየፈነጩና ሕግ እየጣሱ ይገኛሉ።

በመሆኑም ሃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም ግጭት ለመቀስቀስ የሚያደርገውን ጥረት አነሳስና ምክንያት፣ ይህ አዝማሚያ በቸልታ ከታየ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋና አመካከቱን በተመለከተ በግልፅ መወያየትና የጠራ አቋም መያዝ ለኢትዮጵያ ህዝብ ወቅታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ሃይማኖትን በሽፋንነት ለመጠቀም ሲደረግ የቆየው ሙከራ ከተጀመረ የሰነባበተ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የእስልምና ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የሚካሄደው ቅስቀሳና ማነሳሳት ገደቡን አልፎ ሲገለፅ ሰንብቷል።

የሙስሊም ሃይማኖት ሽፋን ያደረጉ የከሰሩ ፖለቲከኞች በበኩላቸው ደግሞ ህዝበ ሙስሊሙን አነሳስቶ ወደ ግጭት ያስገባልናል ያሉትን ስልት ሁሉ ይጠቀማሉ፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ቀደም ሲል ሲደርስበት የነበረውን በደል በማራገብና በመቀስቀስ ከዚህም አልፎ ተገቢነት የሌላቸው አዳዲስ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለማነሳሳትና ለማተራመስ ሲሰሩ ማየት የተለመደ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በትምህርት ቦታዎች መስጊድ እንዲሰራ ደጋግሞ በመወትወት ሃይማኖትና ትምህርትን ለመነጣጠል የተቀመጠውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ለመጣስ ጥረት አድርገዋል፡፡ በአንድ ወቅት ደግሞ በህዝብና ቤት ቆጠራው ላይ የተገኘውን ተጨባጭ ውጤት የሙስሊሙን ማህበረሰብ ሆን ተብሎ ለማሳነስ የተደረገ ተንኮል አስመስለው ማቅረባቸውንም አንዘነጋም፡፡

በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የሚካሄዱት ግጭት የመቀስቀስ ሙከራዎች በቃልና በፅሁፍ ብቻ የተወሰኑ ከመሆን አልፈው ወደተግባርም ተሸጋግረዋል፡፡ሼህ ኑርን ከሰሞኑ ሰለባ ያደረገው

አክራሪነት የት ሊደርስ እንደሚችል ለማወቅም አስቸጋሪ ሆኖብናል። በዚያው ልክ ደግሞ በዜጎች ላይ የህይወት ጉዳትን፣ በንብረት ላይ ወድመትን ከማስከተላቸውም በተጨማሪ ያለመረጋጋትና የስጋት ድባብ እንዲያጠላብን አድርገዋል፡፡ በአንድ አካባቢ የተፈጠረን ግጭት እንደሰበብ በመጠቀምም የበቀል እርምጃ እንዲወሰድ በመገፋፋት ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ እንዲወጣ ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉም ቆይተዋል፡፡ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች አልፎ አልፎ ከተቀሰቀሱትና በአጭር ከተቀጩት ግጭቶች የበለጡ ብዛት ያላቸው ውጥረቶች ወደግጭት ሳይሸጋገሩ እንዲረግቡ በመደረጉ እንጅ እንደ አክራሪዎች ሙከራ ቢሆን ኖሮ ከዚህም የባሰ ግጭትና ደም መፋሰስ በተመለከትን ነበር፡፡

ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የሚካሄዱት ግጭቶች ወይም ግጭት የማነሳሳ ሙከራዎች በተለያየ ደረጃ የሚታይ አሉታዊ ውጤት የሚኖራቸው መሆኑ አይቀርም፡፡ ግጭቶች በትንሽ በትንሹ ብቻ የሚከሰቱ ከሆነ ምን ጊዜም ቢሆን የስጋት መንፈስ መፍጠራቸውና ተጨባጭ ጉዳት ማስከተላቸው አይቀርም፡፡ ትንንሽ የሚመስሉ ነገር ግን ደግሞ በየእለቱ የሚደጋገሙ የግጭት ክስተቶች በህዝብ ላይ ከባድ ስነልቦናዊ ተፅእኖ ያሳርፋሉ፡፡ አንዱ ግጭት ለሌላ ግጭት መቀስቀስ በር እየከፈተ ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ሊያደርጉም ይችላሉ፡፡ በዚሁ ልክ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት የጠፋበት አገር መስለን እንድንታይና ገፅታችን እንዲበላሽም ያደርጋሉ፡፡ ከነዚህ ትንንሽና የማያቋርጡ ግጭቶች ባሻገር በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ከፍኛ ግጭት ሲኖር ደግሞ ለበርካታ ህይወት መጥፋት፣ ለከፍተኛ ንብረት ውድመትና በህዝባችን መካከል በቀላሉ የማይበርድና ለቀጣይ ግጭትና ፍጅት በር የሚከፍት የጥፋት መንገድ ይከፈታል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችግር መንስኤና ባህሪያት በትክክል በመገንዘብ ችግሩን ከስረ መሰረቱ መፍታት አንገብጋቢ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ይህን የምልበት ምክንያት ከሰሞኑ እየታዩ በሚገኙት አደገኛ አዝማሚያዎች እና የአክራሪነት ደረጃው ልኩን አልፎ ወደሽብርተኝነት ደረጃ እየተሸጋገረ በመሆኑ ነው።

እንዳስተዋልነው የአክራሪነት ደረጃ ወደሽብርተኝነት እየተሸጋገረ ስለመሆኑ አመላካች የሆኑ ነገሮች ከሠሞኑ በስፋት እየተስተዋሉ ነው፡፡ ይህ አደጋ ደግሞ በጥያቄ አቅራቢዎችና ህገመንግስቱ ተጣሠ በሚሉት ሃይሎች በተለይም መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ ገብቷል በማለት የሚከራከሩት ፓርቲዎችና የሙስሊሙ ማህበረሠብ ተወካይ ነን ባዮች ተመጋግበውና ተደጋግፈው እየሠሩት ያለ በመሆኑ ጉዳዩን አሣሣቢ ያደርገዋል፡፡

የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ለዚህም ማሣያችን ሠልፍና ህዝባዊ ሥብሠባ ያለመኖሩ ነው ሲሉ የነበሩ ፓርቲዎች የራሳቸውን ችግር በምህዳር መጥበብ አስባብ መንግስት ላይ ለማላከክ ቢሞክሩም፤ ከሠሞኑ ባደረጓቸው ሠልፎች ላይ የተስተዋለው ጉዳይ ግን አሣሣቢ የሆነ ነገር ነው፡፡ የፖለቲካና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች አሉኝ፣ እነሡን በአደባባይ አሠማለሁ ቢሉም አንድነት ፓርቲና ሠማያዊ

ፓርቲ ባዘጋጇቸው ሠልፎች ላይ የተስተዋለው ግን ሃይማኖታዊ አጀንዳና የሦላት ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ ከፍ ሲልም በመንግስትና በመንግስት ተቋማት ላይ የተሠነዘሩ ፀያፍ ሥድቦችን ነው ያስተዋልነውና ያደመጥነው፡፡

እራሳቸውን የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አድርገው ለሠየሙት ግለሰቦች ጠበቃ ነኝ የሚሉት ተምም አባቡልጉ  በየጋዜጣና በኒዮሊበራል ሚዲያዎች ላይ "መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል" ሲሉ እንዳልተከራከሩቱ ሁሉ እሣቸውም ከሰሞኑ አንድነት በጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ድርጅታዊ ስብሰባ ለይ እንደ ፓርቲ አባል ተገኝተው "የፀረ ሽብር ህጉ ሊሻር ይገባዋል" ሲሉ አንድነት “የሚሊዮኖች ድምጽ ለነፃነት” በሚል ላዘጋጀው ሠልፍ የመጀመሪያ አጀንዳ ያደረገው ጉዳይ ላይ ትንታኔ መስጠታቸው የእነዚህን ሃይሎች ተመጋጋቢነት እና ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ፓርቲዎቹ "የታሠሩ ጋዜጠኞች ይፈቱ እነርሱ ጋዜጠኞች እንጂ አሸባሪ አይደሉም" ሲሉ በየሠልፋቸው ላይ ቢጮኹም፤ ጋዜጦቹም በተለይ የቀድሞዋ ፍትህና ተቀጽላዎቿ የእነእስክንድርን ነፃነት ቀድመው አውጀው ግን ደግሞ መንግስትን ከፍርድ ቤት ውሣኔ በፊት መፍረድ አትችልም ሲሉ፤ እነርሡ ለህግ የበላይነት ሳይገዙ መንግስትን እንዲገዛ ሲጠይቁ፤ በሁለት ተቃርኖ ሃሳብ ውስጥ እየዋለሉ መሆናቸውን ባይረዱትም የኋላ ኋላ ጉዳዩን የመረመረው ፍርድ ቤት ውሣኔውን ሠጥቷል፡፡  የአዲስ ታይምስ ተቀጽላ  የሆነችውና በቅርብ ጊዜ ለንባብ የበቃችው የእነተመስገን “ፍትህ” ከሠሞኑ ደግሞ “The iron man” "ብርቱው ሠው" ስትል የእስክንድርን ታሪክ የዘረዘረችልን ሲሆን በርግጥም እስክንድር በጋዜጠንነት ካባ ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን መናድ በተሣነው ጊዜ የህቡዕ ድርጅት ለማቋቋም የሄደበትን ርቀት እራሡ “The iron man” ሲል የሠየመው ተመስገን ሃቁን በመዘርዘር የእስክንድርን ማንነት ያጋለጠ ሲሆን በአንፃሩ ግን የተመስገንን ቂልነት የተረዳንበት ጽሁፍ በመሆኑ ታነቡት ዘንድ ጋብዤ ወደ ዋናው ጭብጤ ስመለስ፣

የአክራሪነትን አደጋ ያልተገነዘቡ ለማለት ስለሚያስቸግር የአክራሪነትን አደጋ መገንዘብ ያልፈለጉ ግለሰቦች አሁንም ብዙ ብዙ በማውራትና በማስወራት ላይ የመገኘታቸው ጉዳይ መንግስትን እንዳያዘናጋው ስጋት አለን፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሣያ የሚሆነኝ ደግሞ የሃምሌ 24ቷ የኛ ፕሬስ ጋዜጣ ነፃ ሃሣብ በሚለው ዓምዷ ላይ ሃሠን አሠፋ የተባሉ ግለሠብ “የህዝበ ሙስሊሙ የዓመት ከመንፈቅ ተቃውሞ እና ጥያቄ ለምን አይቋጭም” ሲሉ ያሠፈሩት ጽሁፍ ሢሆን ፀሃፊው ካነሷቸው ጉዮች ላይ መሠረታዊ የሆኑትንና ለእርሣቸው ያልመሠላቸውን ለእኛ ግን የሚመስለንን እና በተጨባጭ አክራሪነት እያደረሠብን ያለውን ፈርጀ ብዙ ስጋትና አደጋ በመላ ምት ሣይሆን ጥናቶችን መሠረት አድርጌ ግለሠቡን ብቻ ሳይሆን የግለሠቡ ዓይነት ሃሣቦችን ለመሞገት እሞክራለሁ፡፡

ስለሆነም ግለሠቡ ከዘረዘሯቸው በርካታ ዝርዝሮች ውስጥ ከርዕሰ ጉዳዬ ጋር የተያያዙትንና መነሻ የሆኑትን ነጥቦች መጀመሪያ አስቀድማለሁኝ፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ገዢ ርዕሥ ሥር ስለአክራሪነት እና አክራሪያን ግራ ተጋብተናል ለሚለው የአቶ ሃሠን ጥያቄዎች ዋናው የፅሑፌ የትኩረት አቅጣጫና ጭብጥ በመሆኑ ጥናትን መሠረት ባደረጉ አስረጂዎች ወደኋላ እከራከራለሁ፡፡ ለአሁኑ ግን እንደወረደና ከርዕሠ ጉዳዬ ጋር ተያያዥ ናቸው ሥል በለየኋቸው ነጥቦች ላይ ግልጽ መጣረሦች ስላሉ ግልጽ ምላሽ ልሥጥ።

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በ81 ሳምንታት ከሃይማኖት እኩልነትና ወዘተ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መጠየቃቸው መብታቸው ተነክቶ ከሆነ ጥሩ ነው፣ ህገመንግስቱም የሚፈቅደው ነው፡፡ ነገር ግን መሠረታዊ የሠብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ በሃይማኖታዊ መድረኮች ላይ ማስተጋባት ተገቢነት የሌለውና ህገመንግስቱን የሚፃረር መሆኑን ፀሃፊው ሊረዱት ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን ጥያቄው ሊኖር አይገባም ማለት ሣይሆን የራሡ ቦታ ያለው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ማለቴ ነው፡፡

ጥያቄው የቀረበበትና እየቀረበ ያለበት መንገድ የሃገሪቱን ህግና ሥርዓት በተለይም ህገ መንግስቱን መሠረት ያደረገ መሆኑ እየተስተዋለ ነው የሚለውም የፀሃፊው ትርክት ሚዛን የማይደፋ ነው፡፡ የሃገሪቱን ህግና ህገመንግስት መሠረት ያደረገ አዋጅ በሃይማኖት መድረክ ላይ ይሠረዝ ማለት አዋጁ ህገ መንግስታዊ መሠረት እንኳ ባይኖረው የተከለከለ እና የመንግስትና የሃይማኖትን ጉዳይ መቀላቀል መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፡፡

ለአህባሽም ሆነ ለየትኛውም ሠላማዊ ለሆነው ሙስሊማዊ አስተምህሮ መሣደብ ነውር በሆነበት አግባብ በጁምዓ ሦላት ላይ መንግስትንና መንግስታዊ ተቋማትን በፀያፍ ቃል መሣደብ በየትኛውም መለኪያ ሠላማዊ አቀራረብ ተብሎ ሊወሠድ አይችልም፡፡ "የአህባሽ አስተምህሮ በሃይል አይጫንብን ሲሉ አህባሽ እንደ አንድ የእምነት አካል እንዳይንቀሳቀስ አልከለከሉም፣" ብሎ ፀሃፊው መደምደሙም የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ የአህባሽን አስተምህሮ የተቀበሉና እራሣቸውን ለማሠልጠን ለሚሹ አማንያን አዳራሽ የፈቀደ መንግስት ላይና አስተምህሮውን ተከታይ የሆኑት ሙስሊሞች ለይ የተወረወረው ድንጋይ ሳያበቃ ወደጥይት ደረጃ መሸጋገሩ በሌሎች የእምነት ነፃነት ውስጥ ጣልቃ ከመግባት ሊቆጠር የማይችልበት አግባብ ምንድን ነው? ፀሃፊው ቀጥለውም "ያለ ሁከትና ግርግር መብታቸውን በመጠየቃቸው በልዩ መዝገብ ላይ መስፈር የሚገባው መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ" ቢሉም ብዙዎች የሚስማሙት በሁከትና ግርግር እንዲሁም በደም የታጀበ ተቃውሞ ስለመሆኑና በዚህም ፀሃፊው ከሚሉት ተቃራኒ በሆነው ጥቁር መዝገብ ላይ መስፈር እንዳለባቸው ነው፡፡

በተክቢራ በመፈክር ነጭና ቢጫ ወረቀት በማውለብለብ የገለፁበትን የተቃውሞ መንገድ እነ አልጀዚራ መዘገባቸውንም ፀሃፊው ተኩራርተውበታል፡፡ ዳሩ ግን የሃገሪቱ መለያ የሆነውን እና የሉዓላዊነታችን መገለጫ የሆነውን ሠንደቅ ዓላማ ቀዳደው ሲያውለበልቡ አልጀዚራ አለማሳየቱ ሳይመዘንና በአንፃሩ የህዝብ የሆነው ኢቲቪ ይህን ማሣየቱ አግባብ አልነበረም እያሉን ከሆነ በእጅጉ ያሳዝናል፣ኢትዮጵያዊነታቸውንም እንድንጠራጠር ያደርገናል ብዬ አስባለሁ።

ለፀሃፊው በህዝብ አመኔታ ያላገኘው ጀሃዳዊ ሀረካት የአልጀዚራ ሽብር አቀጣጣይ ዘገባዎችን ደግሞ አመኔታ ያገኙ አስመስለው ቢያቀርቡም "ህዝብ" የሚለውን ትርጓሜ ፀሃፊው መጀመሪያ ካለመለየታቸው የመጣ ስህተት ይመስለኛል፡፡ በዚህና በሁከት የታጀበው የተቃውሞ ጎራ ውስጥ ያለው አክራሪ በቡድን ከሆነ አመኔታ ያጣው እሺ ልንል እንችላለን፡፡ እንደ ህዝብ ግን ሁሉንም ወክሎ መናገር አሁንም ሌላ ስህተትና በግድ ተከተሉን የሚል የአመለካከት ነፃነትን የሚጋፋ ትርክት ነው፡፡ ፀሃፊው በመቀጠልም "የኢቲቪ ዘገባዎች ቅንብር ናቸው" ሲሉ በግልጽ የሼህ ኑርን ግድያም ቅንብር ነው የሚለውን ለማሥረጽ መንደርደሪያ ሃሣባቸው ስለመሆኑ ድንገት የአልጀዚራን ቅንብር የተመለከትነው ሁሉ የምናውቀው መሆኑንም ባይዘነጉት ጥሩ ነበር፡፡

ፀሃፊው እንቅስቃሴው እንደማይቆም፣እንዲሁም የነሡን ሃሣብ የማይደግፉ ሰዎች መኖራቸውን ማመናቸውና ግን ደግሞ እንደነሡ እንዲሆኑና ወደነሡ አስተሳሰብ እንዲመጡ በግልጽ ጥሪ ማስተላለፋቸው በራሱ በሌሎች የእምነት ነፃነት ጣልቃ እየገቡ ስለመሆናቸው ጥርት ያለ ማረጋገጫ ነው የሚሆነው፡፡

አገራችን አሁንም ቢሆን የሃይማኖት መቻቻልና መከባበር ተምሳሌት ሆና በዓለም የምትጠቀስ አገር ብትሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በነዚህ ፀረ ሰላም ኃይሎች ምክንያት ይህንን መልካም ገጽታ የሚሸረሽሩ ምልክቶች እየተስተዋሉ መጥተዋል። በአገሪቱ በርካታ ተከታዮች ያሏቸው የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ሲሆኑ በእነዚህ ሃይማኖቶች ጥላ ስር የሚገኙት ጥቂት ግለሰቦች በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ የአክራሪነት አስተሳሰቦችን ሲያራምዱ ተስተውሏል። “አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት” በሚለው መፈክር የክርስትና ሃይማኖትን በአገሪቱ የበላይ እንደሆነ አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ ሲንጸባረቅ የነበረበትን ሁኔታ እናስታውሳለን።

ይህ አስተሳሰብ ግን በሃይማኖቱ አባቶች ጥረትና ተቋማዊ እርምጃዎች እየከሰመና እየጠፋ ምናልባትም ከጥቂቶች በጣት ወደሚቆጠሩ ግለሰቦች የወረደ ሃሳብ ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ እስላማዊ መንግስት እስከመመስረት የሚደርስ ዓላማን እናሳካለን በሚል ከውጭ ሃይሎች ከሚደረግላቸው ድጎማና ይህ ጉዳይም የከሰሩ ፖለቲከኞች አጀንዳ መሆን ጋር ተያየይዞ መንግስት ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገ ተከታታይና የማያዳግም እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ለሆደ ሰፊነት ቅድሚያ በመስጠት ከዛሬ ነገ ይማራሉ በሚል ያልተገባ አካሄድ ለማስታመም በመሞከሩ መነሻነት

ጥቂቶቹ እየበዙ፣ ከድንጋይ ወደ ጦር መሳሪያ እየተሸጋገሩ እና የሀገሪቱን መለያና ሉዓላዊ መገለጫ የሆነ ክቡር ሰንደቅ ዓላማ እስከመቀዳደድ መደረሱ በፍጹም በቸልታ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነው።

በአገሪቱ ስር ሰዶ የቆየውን የሃይማኖት መቻቻልና መከባበር ይበልጥ ለማጎልበት የሚያግዙ ጉባኤዎች የተካሄዱ ቢሆኑም እየታዩ ያሉ የአክራሪነት እንቅስቃሴ እንወክለዋለን ለሚሉት ሃይማኖትም ጭምር የማይበጅና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ በግልፅ እየታወቀና የሃይማኖት አባቶችን የጥይት ሰለባ እስኪያደርግ ድረስ የዘለቀ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ግን መንግስት ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገ ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት የብዙዎች ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ሁሉ ጥያቄ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የታደሉትና ከኛ ትምህርት የወሰዱት ለወትሮው ግጭት የማይለያቸው አገራት ዛሬ በየሃይማኖታቸው ፀንተው በአገራቸው ሰላምና ልማት ላይ እንደ አንድ ቤተሰብ ሆነው በመስራት ላይ በሚገኙበት በዚህ ጊዜ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ እኛ ወደኋላ የመሄድ አዝማሚያ ላይ መገኘታችን በእውነቱ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ነው።

በአገራችን የሃይማኖት አክራሪነት ያልነበረና ከውጭ የመጣ አደገኛ አዝማሚያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት እጅግ ብርቱ ነው። በመፅሃፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱስ ቁርዓን ሰውን መግደል ሃጢያት መሆኑ ግልፅ በሆነበት አግባብ የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት ተቃራኒ የሆኑና ክፉ መንፈስ ያደረባቸው አክራሪዎች የእሳት ዳር ጨዋታ ሲጀምሩ ጉዳዩ በቀላሉ መታለፍ አይኖርበትም የሚለው ዛሬ ዛሬ የብዙዎች ድምጽ ነው። መንግሥት ከህብረተሰቡ ጋር ተባብሮ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ የሕግ የበላይነትን የማስጠበቅና የዜጎቹን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።

እናቶቻችን እና አባቶቻችን ይችን ሀገር ጠብቀው ለማቆየት ከፍተኛ መስዋእትነት መክፈላቸው ይታወቃል። በሰላም አብሮና ተቻችሎ የመኖር እሴትንም አስረክበውን አልፈዋል። ሰዎች የሚያራምዱት የተለያየ እምነት በደስታም ይሁን በሀዘን ጊዜ ከመደጋገፍ አላገዳቸውም። ይህ በሰላም አብሮ የመኖር እሴት ለዚህ ትውልድ ታላቅ መሰረት የሆነውንና ለእምነት ነፃነት መከበር ዋስትና የሰጠውን ህገመንግስት አክብረንና አስከብረን ለተተኪው ትውልድ የማውረስ የትውልድ አደራ እንዳለብን በውል ልንረዳ ይገባል።

ደሴ ውስጥ የሼህ ኑርን  መገደል መንግስት  ለህዝብ ግንኙነትና ለፕሮፖጋንዳ ግብአትነት እየተጠቀመበት ነው ነው የሚለው የአክራሪዎችና የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆች የጋራ ልፈፋ እውነታውን ፈጽሞ ሊያደበዝዘው አይችልም። መንግስት ወንጀልን የመከላከልና ወንጀል የሰሩትን በፍርድ አደባባይ የማቆም ሃላፊነቱን በጣልቃ ገብነት ቢፈርጁትም በአንፃሩ እነሱ በጠሩት ሰላማዊ ሰልፍ ሶላት እየሰገዱና የአክራሪነትን አጀንዳ እያስተጋቡ በአደባባይ የታዩት ራሳቸው መሆናቸውን ከቶ እንደምን አድረገው ሊያስተባብሉት ይችላሉ?  አክራሪ ፖለቲከኞቹም የአሸባሪዎችን አጀንዳ በዋነኝነት ማራገባቸውና  ዋና መፈክር ማድረጋቸው ማን በማን ውስጥ ጣልቃ እየገባ መሆኑንም የሚያረጋግጥ በመሆኑ መንግስት ለእነዚህ የከሰሩ ፖለቲከኞች ሳይበገርና ቂብ ሳይሰጥ ህገመንግስቱ በፈቀደለት አግባብ ሁሉ ከህብረተሰቡ ጋር ተባብሮ መስራት ይጠበቅበታል።

ከ “አኬልዳማ” ፊልም ወይስ የፍርድ ውሳኔ?፣ “አኬልዳማ”ው የአይሁድ ወይስ የኢ.ህአዴግ?፣ የሽብርተኝነት ፖለቲካ እና የአቶ መለስ ጨዋታ “ሙሽራዬ ቀረ”፣ ከጎሳ ልዩነት ወደ ሃይማኖት ልዩነት? ያዋጣል?፤ የተባበሩ ጨኸቶች ቦአዚዝ፣ መጅሊስ፣ መምህራን ------፣ ሶስቱ የእስልምና ንቅናቄዎች እና ፖለቲካዊ እንድምታቸው፣ እስከ "ኢ.ህአዴግ ክርስቲያኖችን የሚያስፈራራበት ምናባዊ ጭራቅ “ወሃቢያ” የሚሉት መጣጥፎች በቀድሞዋ ፍትህ ጋዜጣ ላይ ለንባብ የበቁና በመንደር የተጀመረው አክራሪነትና ምናባዊ የተባለው ጭራቅ በተግባር አደባባይ ወጥቶ እንዲገለጽ ያደረጉ ፀረ-ህገመንግስታዊ መጣጥፎች የነበሩ ሲሆን፤ አሁን በአደባባይ አፍጦ የመጣው አክራሪነት በሰላማዊ ሰልፍ ሳይታጠር ፍትህ በጀመረችው ፀረ-ህገመንግስታዊ ዘመቻ ታግዞና በኋላም አዲስ ታይምስ መጽሄት በአኬልዳማው የጀመረችውን መዝሙር በጀሃዳዊ ሃረካት ላይ መድገሟን ተንተርሶ እዚህ ደርሷልና "ሳይቃጠል በቅጠል" እንደሚባለው የአክራሪዎች እንቅስቃሴ ልጓም ሊበጅለት ይገባል።